ስኩል ኦፍ ቱሞሮ
አዲስ አበባ
የአማርኛ ትምህርት 9ኛ ክፍል አጫጭር ማስታምሻ እና ጥያቄዎች

ክፍለ ጊዜ -2

የቃላት መጥበቅና መላላት

በአማርኛ ቋንቋ አንዳንድ ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የተለያዩ ፍች ይሰጣሉ።እንደነዚህ አይነት ቃላት በተናጠል ሲታዩ የትኛውን ፍች እንደያዙ ወይም ጠብቀው ይሁን ላልተው እንዲሚነበቡ ለመለየት ያስቸግራሉ። ለዚህም በ አ.ነገር ውስጥ ሲገቡ እንደተጠቀምናቸው አገባብ መለየት ያስችለናል።

በአማርኛ ቋንቋ ባለ ሦስት እግር ቃላት ብዙውን ጊዜ የሚጠብቀው ድምፅ የመካከለኛው ነው።አልፎ አልፎ የመጨረሻው ድምፅም የሚጠብቅበት ጊዜ አለ። ነገር ግን በአማርኛ የቃል መጀመሪያ ድምፅ አይጠብቅም።

ምሳሌ፦ ፩, ሰላም የክፍሉ "ዋና" አለቃ ናት።(እዚህ ላይ ዋና ጠብቆ ይነበባል)

፪, ሄኖክ ውሃ "ዋና" ይችላል።(እዚህ ላይ ደግሞ ላልቶ ይነበባል ማለት ነው።)

<u>የቤት ስራ ጥያቄዎች</u>

ሀ. <u>ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የሚኖራቸውን ፍች አመልክቱ!</u>

፩,አለ (ሲጠብቅ)----------

(ሲላላ)----------

፪, አጣና (ሲጠብቅ)----------'----------

(ሲላላ)----------

፫, አካፋ(ሲጠብቅ)----------

(ሲላላ)----------

፬, አላት(ሲጠብቅ)----------

(ሲላላ)----------''----------

፭,ጠላት(ሲጠብቅ)----------

(ሲላላ)----------

፮, አያት(ሲጠብቅ)----------

(ሲላላ)----------

ለ. <u>ቀጥሎ በቀረቡ አ.ነገሮች በትዕምርተ-ጥቅስ ውስጥ የገቡት ቃላት ጠብቀው ወይም ላልተው መነበባቸውን ለዩ!</u>

፩, የ"አባይ" ግድብ መገንባት ለሀገራችን ትልቅ እምርታ ነው።።

፪, ሄኖክ ራሱ "በራ" ስለሆነ ኮፍያ ማድረግ ያዘወትራል።።

፫, መብራቱ በዘጠኝ ሰዐት "በራ"።።

፬, አለሙ በ"ሰባ" ብር ትልቅ ዳቦ ገዛ።።

"ርቀታችንን በመጠበቅ እጃችንን በተገቢው በሳሙና በመታጠብ ራሳችንን ከኮሮና እንከላከል"

መልካም ስራ